# የጋራ ሀገርን ለማዳን ፤ የጋራ ዓላማ መኖር የተቃዋሚዎች ግዴታ ነው

ሐተታ ቁ. 4

ሰኔ 2006 ዓም

ኢትዮጵያ የጋራችን ነች ብሎ ከልብ የሚያምን ዜጋ ሁሉ፤ በአንድ ጉዳይ ላይ በግድ መስማማት ይጠበቅበታል። የቅድሚያ ግዴታው ሊሆን የሚገባው የጋራ ሀገርን ለማዳን የጋራ ዓላማ ሊኖረው የግድ ይላል የሚለውን መቀበል ነው። በጋራ ዓላማ ላይ በመነሳት የጋራ ራዕይን ለማስተናገድ መቻል፤ ሀገራችን የጋራችን ነች ለሚለው መርኅ መሠረት ይሆናል። የጋራ ሀገር አለን የሚለው አባባል ተርጉም የሚኖረውም፤ በጋራ ዓላማና ግብ ላይ መተባበርና መረባረብ ሲቻል ብቻ ነው። ዕምነትን በተግባር ካልተረጎሙት ፤ ዕምነትን ማመኑ ብቻውን ሥርዔት እንድማያስገኝ የታወቀ ኩነት ነው።፤ በዕምነት ላይ ብቻ ተስፋ ማድረግ ደግሞ፤ ውጤቱ ምኞት በቻ ሆኖ ይቀራል። ምኞትና ተስፋ ተባብረው ዉጤት የሚያስመዝግቡት፤ በብርቱ ሥራና ተግባር ሲደግፉ በቻ ነው ። እንከን-የለሽ ምግባርና ብርቱ ተግባር፤ ሀገር ለማዳን የሚታገለው የአንድነት ኃይል ሊኖሩት ይገባል። ለዚህም እኮ ነው፤ ቀደምት ወላጆች " **ምኞት አበባ ነው ፤ መስራት ግን ፍሬ ነው።** " የሚል ይትብሃል አስመዝግበውልን ያለፉት። የወሬ የለው ፍሬ፤ የአበባ የለው ገልባ፤ ተብሎ እንዳይፌዝብን ከተፈለገ፤ ቃለ- ንባብን ከተግባር ጋር አዋኀዶ መታገል ግዴታ ይሆንብናል። በተለያየ ፅንሰ- ኃሳብ ላይ መገባባት ሊኖር ይችላል ተብሎ ባይገመትም፤ ሀገርን በማዳን ትግል ላይ ግን ሁሉም ተመሳሳይ ዓላማና ግብ ሊኖረው ይገባል።

የጋራ ሀገራችን የሆነችውን ኢትዮጵጵያ ማዳን አለብን ብሎ የሚታገል የተቃዋሚ ኃይል፤ የጋራ ዕቅድና ስልት ነድፎ ከመተባበር የተለየ መርጫ አይኖረዉም። ይኽ ሀቅ ደግሞ እስኪያሰለች ድረስ ተደጋግሞ- ተደጋግሞ የተባለለት ጉዳይ ነው። እስካሁን ግን ይህንን በተግባር መለወጡ ቀርቶ፤ ዕርባና ያለው የጋራ ትግል ስልትና ስትራተጅ እንኳን ተነድፎ አልታየም። በተግባርም አልዋለም። ይኽ እስካለተከሰተ ደረስ ደግሞ ወያኔን ማንበርከክ ቅርቶ ማስደንግጥ እንኳን የሚቻል አይሆንም። የምትታገለውን ጠላት ማንነት በሚገባ መረዳት፤ ትግልህን አጠናክረህ ለመታገል እንደ መጀመሪያ ርምጃ ይቆጠርልሀል። ትንታኔንና ግምገማን፤ በምኞትና በይሆናል ላይ ከመሰረቱት ፤ ተጨባጩን ሁኔታ ለማየት ይከለክላል።

የኢትዮጵያ አጥፊዎች ዎያኔና ተባባሪዎቹ ፤ ሀገራችንን ለማጥፋት ሲሉ ብቻ የጋራ ዓላማ ስለነበራቸው ፤ በዚህ ዕኩይ ተግባር ዙሪያ ብቻ ለመተባበር በቅተው ዕቅዳቸውን በተግባር እየተረጎሙ ይገኛሉ። ይህንን መራራ ኮሶ እየጎመዘዘም ቢሆን መዋጥ ሊኖርብን ነው። ምክንያቱም መራራው ዕንክብል ከተዋጠ፤ የሀገሪቱን ተውሳኮች ጠራርጎ ለማውጣት ፍቱን መዳህኒት ነውና ! አጥፊዎቿ፤ እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት ተባብረው ዕቅዳቸውን ሲያስፈጽሙ፤ ኢትዮጵያን ማዳን አለብን ብሎ የሚታገለው የአንድነት ኃይሉ ለምን እስከ ዛሬ ድረስ ለመተባበር እንዳልቻለ የሁሉም ዜጋ እንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል።

በዕርግጥም ሲታይ፤ ይህ የአሁኑ ተጫባጭ ሁኔታ፤ የአንድነቱ ኃይል መተባበር አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምን ጊዜውም በበለጠ ይፈልገዋል። ዓግቶም ይጠብቀዋል። " **ውሾችም ይጮሃሉ፤ ገመሎቹም ይጓዛሉ**! " የሚለው የወያኔ ምፀትና የትዕቢት አነጋገር አንገሽግሾታል። መረሮታል። ይህን የሕዝብ መነገሽገሽና መማረር የአንድነት ኃይሉ የቱን ያህል እንደሚጋራ ግን በዕርግጥኝነት መናገር ያስቸግራል። ያማ ቢሆን ኖሮ፤ ባሁኑ ወቅት፤ ትግሉ በአስተማማኝ ደረጃ ላይ በተገኘ ነበር። ዛሬ ህዝቡ የሚያዝነውና የሚንገሸገሸው ዎያኔዎች በሚያወርዱብት ጭቆና ብቻ ሳይሆን፤ በአንድነት ኃይሉ ባለመተባበርና ያመረቃ ውጤት ባለማስመዝገቡም ጭምር መሆኑ የሚካድ አይሆንም።

የአንድነቱ ኃይል የሕዝቡን መበደልና ማዘን ከልብ ሊረዳውና ሊገነዘበው ይገባል። ይህም ማለት፤ ጥቃት ያላንገሸገሸው፤ ውርደት ያላንገበገበውና በደል ያላንገፈገው ኃይል ደግሞ፤ ከሙታን በላይ፤ ከህያው በታች እንደሚኖር ሊረዳው ይገባል ማለት ነው። ከሙታኑ በላይ ከኀያው በታች ደረጃ ከተደረሰ ደግሞ፤ የነጻነት ትግል እንቅስቃሴ የደረጋል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። ምድረ-ተገንጣይ መንጋ እኮ ፤ **ከተት! መክት** ! ብሎ ነው ትግሉን የጀመረው ። ይህን እየከተቱ መመከት የሚለውን ስልት አንግቦ የሚታገል ኃይል ደግሞ ጠላቱን እያንበረከከ ድልን እንደሚቀዳች መጠራጠር አይቻልም። በመሆኑም፤ የአንድነት ኃይሉ፤ **ተስማምተህ ከተት! ተባብረህ መክት** ! የሚል ብሄራዊ የኅብረት ጥሪ እያስተጋባ

መታገል የቅድሚያው አጀንዳ ሊሆን ይገባል ። እንደ ጥንት አንደ ጧቱ፤ እንደ አባት-አደሩና ብሎም፤ እንደ ቀደምት-ታሪኩ፤ ይህ የዛሬው ትውልድ ለሀገሩ ነጻነትና ክብር ለራሱ ህይወትና ማንነት ሲል ፤ ለብሄራዊ ነፃነት ትግል መነሳት አለበት ! ይህ ሳይሆን ቀርቶ፤ ሀገሪቱ ወደ ውድቀቷ ጠርዝ ከደረሰች በኋላ፤ ከታሪክና ትውልድ ተጠያቂነት ለመምለጥ ሲባል፤ አንዱ በሌላው ላይ ጣት መጠቋቆሙ ማንንንም አይረዳ። ሀገርንም አይጠቅም።

አዳም በሄዋን፤ ሄዋን በእባቧ አሳሳችነት ቢያመካኙት ከተጠያቂነት አያስመልጥም ! በሀገሪቱ ላይ ለሚመጣው ጥፋት፤ ቀጥታ ተጠያቂዎቹ ዎያኔና ተባባሪዎቹ እንደሚሆኑ ባያጠያይቅም፤ ዳር ተቀምጦ በአርምሞ የሚመለከተው ሁሉ ከታሪክና ከትውልድ ፍርድ የሚያመልጥ አይሆንም።

የአንድ ሀገር ዜጋ፤ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ሊሰማው የሚችለው፤ በመጀመሪያ ደረጃ የራሱ ተገዥ ሆኖ የኅሊና ነጻነቱን ሲያስከብር ለመሆኑ፤ የሞራል ሥልጣንና ልዕልና ያላቸው ሰዎች ያስተምራሉ። አስተምህሯቸውንም በዓርዓያነት የገልጻሉ። የዘር ፖለቲካ በሰፈነባት በዛሪይቱ ኢትዮጵያ፤ ዜጎቿን ፤ በዘርና ቋንቋ፤ በሃይማኖትና በጎሳ ሊከፋፍሉ የሚጣጣሩትን ለመቋቋም በሚደረገው ትግል፤ የኢትዮጵያን ትንሣዔ የሚመኝ ሁሉ የጋራ ርብርቦሽ ሊያደርግ ይጠበቅበታል። ይህም የኢትዮጵያን ዘር ከመቅሰፍት እንደመጠበቅ ይቆጠራል። ይሁንና፤ ይኽ እንደ ማጨረሻ ምዕራፍ መታየት የለበትም። ትግላችንን እየቀጠልን በሄድን ቁጥር ግን ሊያደፋፈረን የሚችል ተጨማሪ ምዕራፍ ይሆናል።

በመሆኑም፤ የዘር ፖለቲካው ግብዐተ-መሬት እስካገኘ ደረስ ትግሉ የሚቀጥል ይሆናል። አዲስ ጉልበት አዲስ ስልት ፤ ያልጥቆጠበ ጥረትና የተራቀቀ ስትራተጂ አስፈላጊዎች ይሆናሉ። ለዚህ መሠረቱ ደግሞ፤ በመተማመን ላይ የተገነባ የኅብረት ትግል ማካሄድ ለመሆኑ አያከራክርም።

አንድ አገልጋይ፤ ለሁለት ጌቶቹ ( አለቆቹ) በዕኩል ታማኝነት አገልግሎት ለማስጠት እንደማይቻለው ሁሉ፤ ተቀዋሚ ኃይል ነኝ የሚለውም ፤ ሁለት ልብ ይዞ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችል ትግል ማመድረግ አይሆንለትም። ከሁለት ጎራዎች አንዱን መምረጥ አለበት። በወያኔ ብብት ተለጥፎ ህዝብን ነጻ ማውጣት የሚቻል አይሆንም። ወያኔን በምርጫ አሸንፌ ሥልጣን እይዛልሁ የሚለው ህልም፤ ቅዠት ሆኖ መቅረቱን ያለፉት ሀያ ሦስት ዓመታት በማያወላውል ፊርማ አረጋግጠዋል። ይህንን ሀቅ፤ ለሚቅጥለው የዎያኔ መርጫ ወድድር የሚዘጋጁት ሁሉ ሊረዱት ይገባቸዋል።

የሚኖሩት መርጫዎች ሁለት በቻ ናቸው። አንደኛው በዎያኔ ድባብ ዙሪያ እየተሽከረከሩና እየተልፈሰፈሱ ከማይቀረው የሀገር ጠላቶች ጋር አብሮ መከሰም። ሁለተኛው፤ የሕዝብና የሀገር ወገን ሆኖ በዕምነት ፀንቶ፤ ሀገርን ከጥፋት አድኖ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ይሆናል። ትግልን በዘማዊነት ሊያካሂዱት የሚገባ መርኅ አይደለም። "**እስከ መጨረሻው ያመኑ ብጹዓን ናቸውና** " ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ማዳን የሚቻለው፤ እስከ መጨረሻው በዕምነት ጸንቶ በመታገል ብቻ ይሆናል። በአኩሪ ታሪኩ ለሚኮራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ማስተውሱ፤ ምጥን ለናቷ ማስተማር ይሆናል። ታዲያ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውንተኞቹን ልጆቹን ከአስማሳዮቹ ለይቶ የሚያውቅበት የራሱ አዕምሮ አለው።

የሰብዓዊነት ክብር፤ የሞራልና የህግ አቋሞች፤ ባኅላዊና ታሪካዊ ተቋማት እየተራቁቱና እየከሰሙ በሚሄዱባት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ በድኅረ- ዎያኔ የሚከሰተውን ሁኔታ አስቅድሞ ማሰብና መፍተሄውን ማዘጋጅትም የትግሉ አካል ሆኖ መታየት የገባዋል ። አንድን ፀረ ሕዝብ ሥረዓት ለማስወገድ በሚደረገው የትግል ሂደት ቅድሚያ የሚሰጠው ርብርቦሽ ፤ ያን ሥርዓት በመገርሰሱ ላይ መሆኑ ባይዘነጋም፤ አብሮ ጎን ልጎን መታሰብ የሚገባው ዓብይ ጉዳይ ግን የሀገሪቱን የወደፊት ዕድል በብሩኅ ተስፋ መቅየስ ይሆናል። ማፍረስ እንደ መገንባት ቀላል ስለማይሆን፤ ሀገርን የመገንባቱ ተግባር አስቅድሞ ሊታሰብበት ይገባል። አምባገነንን መጣል ብቻውን በቂ ሊሆን አይችልም። ከአድማስ ባሻገር ማሰብ መጀመር ከአሁኑ ነው።

ባለፉት አርባ ዓመታት ሦስት ሥርዓቶች እየውደቁ በአዲስ አምባገነን መተካታቸውን ተመልክተናል። የሚወድቀው አምባገነን ጦሱን ይዞ ሲሄድ ግን ተተኪው አምባገነን ካለፈው የባሰ እንጅ የተሻለ ሆኖ አልተገኘም። የኢትዮጵያ ህዝብ ልዩ ልዩ ትግሎች፤ በየወቅቱ የሚነሱትን ጭቋኝ ሥርዓቶች ማስወገድ ቢቻላቸውም፤ እናም ደግሞ፤ የአንዱ አምባገነን ሥርዓት መንኮታኮት ህዝቡን ቢያስደስተውም፤ በተሻለ ሥርዓት ለመተካት ግን እስካሁን አልታደለም። የመሬት ላራሹን መፈክር አንግቦ የታገለው ህዝባዊ አምፅ፤ የመሬትን ይዞታ ለገበሬዎች እንዲተላለፍ ማደረጉ ቢያረካውም፤ የዛሬዎቹ አምባገነኖች ግን ጭራሹኑ የሀገሪቱን ለምና ሰፋፊ የርሻ መሬቶች ለውጭ ባዕድን እየቸበቸቡት ይገኛሉ። ይኽም ኩነት፤ የሚመጣው ለውጥ ሁሉ፤ ያለፈን መከራና ፍዳ የሚያስረሳ ሳይሆን፤ እንዲያውም፤ በተተኪው ላይ እያመጸ ትግሉን

በአዲስ ጥርስ እንዳገና ሀ ብሎ እንዲጀምር ያስገደዳል። ይኽም በበኩሉ ሕዝቡን ለሌላ ዙር መከራና ስቃይ እየዳረገ አዲስ መሥዋእት እንዲከፍል ይዳርገዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኅይዎቱንና ዕድሜውን በሙሉ አምባገነንን እያታገለ መኖር አለበት ተብሎ የተፈረደበት ይመስል፤ የአምባገነን ገዥዎች መፈራረቂያ ሆኗል። የሚያደርገው ትግል ሁሉ፤ መቅኖ ያጣ ልፋት በመሆኑ፤ የደሞክራሲ አስተዳደር ለማምጣት የተደረገው ጥርት ሁሉ የውሃ ሽታ እየሆነ ቀርቷል። ከዚህ ማለቂያና መቋጫ ካለተገኛለት አዙሪት ለመውጣት ግን እስካሁን አስተማማኝ መፍተሄ አልተገኘም። የመፍተሄውን ፍሊጋ ለመውሰድ ኃላፊንቱን ሊቀበል የተዘጋጀ ወገንም እኔ አልሁ ብሎ ድምጹን አላሰማም። ዛሬ በትግሉ ሂደት ድምጹን ያላሰማ ዜጋ፤ የድል አጥቢያ አርበኛ ለመሆን ያሰበ እንዳያስመስልበት ፤ በሀገሪቱ ችግር መፍተሄ ፍልጋ ላይ እንዲያተኩር የዜግነት ግዴታ አለበት ። ይህንን ለማለት የሚችሉ፤ የሞራል ብቃት ያላቸው ዜጎች እንደሚኖሯት ኢትዮጵያ ዕምነት አላት። ውሉ እንደጠፋበት ልቂቂት የተጥመለመለውንና የተወሳሰበውን የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግር ለመፍታት፤ ሁሉ-አቀፍ አመለካከትና ስትራተጂያዊ ራዕይ ያላቸው የአንድነት ኃይሎች ተሰባስበው መውያየትና ከጋራ ውሳኔ ላይ መድረስ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ጉዳይ ይውል-ይደር የሚባልበት ሳይሆን፤ ባንገብጋቢነት ደርጃ የሚታይና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ብሄራዊ የትግል አጀንዳ መሆን አለበት ።

ወጣቱ ትውልድ ጀግኖችንና ታጋዮችን ይፈልጋል። ለመሥዋዕትነት ዓርዓያ የሚሆኑትንም ለማይትና ለማመን ይጓጓል። የጥንቱን አኩሪ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ የወቅቱን የዓለም አቅፍ፤ አህጉራዊና የሀገር ውስጥ ተጫባጭ ሁኔታዎች መረዳትን ይመኛል። ትላንት ፤ በደርግ ፋሽስታዊ አገዛዝ ስር በአሰቃቂ ሁኔታ ማደጉ አንሶት፤ ዛሬም በዎያኔ የዘረኛ አገዛዝ በመውደቁ ምክንያት የህይወት መልኅቅ እንዳይኖረው ሆኗል። ቅደም ብሎ ከእርሱ በፊት የነበረው ያ ቆራጥ መሥዋዕታዊ ትውልድ፤ በደርግ ጥይት የተጨፈጨፈውን ጓደኛውን ለማንሳት ምን ያህል የሞራል ብርታትና የጀግንነት ብቃት እንደነበረው እድሜው ፈቅዶለት ለማየት ባይችልም እንኳ፤ ከወላጆቹና ከታትላላቅ ወንድም-እህቶቹ ተነግሮታል።

ይህ የሚያመለክተው ፤ ኢትዮጵያውያን ፤ በተጋነነና ስሜታዊ በሆነ ታሪክ የተገነባን ሕዝቦች አለምሆናችንን ያስረዳል ። ይኽም፤ **" የኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ መቶ ዓመት አይበልጥም ። " የሚለውን የዎያኔን ክኅደት ድምጥማጡን ያጠፋዋል።** ወጣቱ ትውልድ ፤ ለሀገሩ የአኩሪ ታሪክ ትንሣዔ ቆርጦ መነሳት የጠበቅበታል !

ላለፉት አርባ ዓመታት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ከከባድ ፈትናዎች ጋር የተጋፈጠባቸውና እንዲያውም ተስፋ አስቆርጭ ሁኔታዎችን የተጋተረባቸው ክስተቶች ነበሩ። የውጭ ጠላቶቿና ተፎካካሪዎቿም የነጠረውንና ትክክለኛውን ታሪኳን እስከ መዘንጋት ደርሰው እንደነበር ይገመታል። ሕዝቧንም ብቸኛ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ሀገሪቱንም በመያገና ለመሥዋዕት ጠቦት ለማቀረብ የተደረገውን ሞከራ በዎያኔ ጋሻጃግሬነት ሲከናውን ተመልክተናል። በጠላቶቻችንም አመለካከት፤ ደካሞች፤ ኅስቋሎች ያልሆንና፤ በፍርሃትም የማንርበደበድ፤ የማንሽመደመድና የማንበገር መሆናችንን አሳይተናል። ከዚህም በቀር፤ ለሚጠበቁብን ሀገራዊ ግዳጆች ሁሉ፤ ምን ጊዜም ዝግጁዎች እንደሆንና የሞራል ግዴታና ኃላፊነት ያለብን መሆናችንን አስማስከረናል ። ይኽ ግን ራሱ በቂ እንዳልሆነ እንገነዘባለን ።

<u>ኢትዮጵያውያን፤ በተለይም ይኽ የዛሬው ትውልድ ማነነቱን ሊያስማስከር የሚችለው፤ ዘርኞቹ በዘረጉት ሥርዓት የምትከፋፈለዋን ሀገሩን አድኖ ደሞክራሲያዊ ሥርዓት በመመስረት ሕዝቡን ከማከራ ቅንበር ነጻ ለማውጣት ሲችል ብቻ ነው።</u> ይህ ደግሞ ዕውን የሚሆንበት ወቅቱ ሩቅ አይሆንም። ይህንን በሚገባ ከተገዘብን ዘንዳ፤ አሁን ምን ማደረግ አለብን ? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ ለመውያየት ነጻ መድረኩን ተጠቅሞ፤ ተቃዋሚው ክፍልና ሕዝቡ ተወያይቶ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ይጠበቅበታል። በበኩላችን ግን በሚከተሉት ዐውደ-ኃሳቦች ላይ፤ የተባ ውይይት ማደረግ ለአንድነት ኃይሉ መተባበር መርኅ ይሆናል ብለን እናስባለን። እናምናለንም።

<u>መሠረታዊ / መተከላዊ ጉዳዮች፡--</u>

1. በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድንትና ለዕልና፤ በዜጎቿ ዕኩልነትና ነጻነት፤ በምልካ ምድሯ ልዋላዊነት የማይደራደር፤

2. በደሞክራሲ ሥርዓት፤ በመድበለ ፓርቲ ቀመር፤ በህግ የበላይነት፤ በዘርና በቋንቋ ላይ ያልተመሰረተ ፈደራላዊ ሥርዓት የሚያምን፤

3. የኢትዮጵያ ሕዝብ ፦ በሀገሪቱ ከርሰ- ምድርና በመሬቷ ላይ ያሉት ብሄራዊ ሃብቶች ላይ ባለቤት መሆኑና ዕኩል ተጠቃሚ እንደሆነ አምኖ የሚታገል፤

4. የአንድነት ኃይሉን ትብብር ከልብ እንደግፋለን የሚሉ ኢትዮጵያውያን/ያት አዛውንት፤ የሽምግልና ሚና እንዲጫዎቱ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !

////////////////////////////-------------------- \\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\\